አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር 22, ጥቅምት 2015 ዓ.ም Issue No. 22, October 2022

# አዋሽ ዜና መጽሔት

# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Marketing & Communication Directorate

# ታታሪዎቹ
# TATARIWOCHU
Empowering The Visionaries



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980
www.awashbank.com

ዋና አዘጋጅ: ተሾመ ዋቅጅራ
ረዳት አዘጋጆች: ድሪባ መገርሳ
ሰላም ተክለጽዮን

ፎቶግራፍ: ዳንኤል ምትኩ

EDITOR-IN-CHIEF: Teshome Wakjera
ASSISTANT EDITORS: Selam Tekletsion
Deriba Megerssa
PHOTOGRAPHER: Daniel Mitiku

8980
12638
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com
SWIFT Code: AWINETAA

# በዚህ እትም


አዋሽ ባንክ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የብር 5 ሚሊየን ድጋፍ አደረገ ... 1
አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አረንገዷዴ አሻራቸውን አኖሩ ... 2
አዋሽ ባንክ እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት በጋራ ለመስራት ስምምነት ተፈራረሙ ... 3
አዋሽ ባንክ የታታሪዎቹ የስራ ፈጠራ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና አካሄደ ... 4
አዋሽ ባንክ በከባድ ዝናብ ቤታቸው ለወደመባቸው አርሶ አደሮች ድጋፍ አደረገ ... 5
አዋሽ ባንክ ከዘጠኝ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ጋር ያደረገው የብድር አቅርቦት ስምምነት ... 6
አዋሽ ባንክ የዲጂታል ትምህርት አስተዳደር መተግበሪያ ቴክኖሎጂን ይፋ አደረገ ... 7
አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመተባበር አዋሽ ሼባማይልስ ካርድን በስራ ላይ አዋለ ... 8
ዘመናዊ ስልክ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር የጥቃት አይነቶች የትኞቹ ናቸው? ... 9
በዘመናዊ ስልኮች ላይ ያሉ ክፍተቶች እና የሚያመጡት አሉታዊ ተፅዕኖዎች ... 10

# IN THIS ISSUE

Quotes ... 11
Photo Reel ... 12

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# አዋሽ ባንክ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የብር 5 ሚሊየን ድጋፍ አደረገ




የድጋፍ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

አዋሽ ባንክ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት የብር 5 ሚሊየን ድጋፍ አድርጓል።
የክልሉ የመንግስት ዋና ተጠሪ ጸጋዬ ማሞ እንደገለጹት የክልሉ መንግስት ተልዕኮዎችን ለማስፈጸም የአጋሮችን ድጋፍ በመጠየቅ ሃብት የማሰባሰብ ስራ መሰራቱን የገለፁ ሲሆን ባንኩ ላደረገው ድጋፍ በማመስገን ባንኩ በክልል ለሚሰራቸው ስራዎች መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

የአዋሽ ባንክ ደቡብ ምዕራብ ሪጅን ዋና ዳይሬክተር ይርጋ ይገዙ በበኩላቸው የአዋሽ ባንክ ደቡብ ምዕራብ ሪጅን ክልላዊና ሀገራዊ ጥሪዎችን በመቀበል አስፈላጊውን ትብብር ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሰው፣ባንኩ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት መነሻ የሚሆን የ5 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ከማድረጉም በተጨማሪ በቀጣይም ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

አዋሽ ባንክ ከምስረታው ጀምሮ የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረጉም ባሻገር ለማህበረሰቡ እገዛና ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

# አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አረንገጓዴ አሻራቸውን አኖሩ




የአረንጓዴ አሻራ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

የእህት ኩባንያዎቹ አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ሠራተኞች ሐምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ፅ/ቤት ጋር በመተባበር 20 ሺህ ችግኞችን በመትከል አረንጓዴ አሻራቸውን አኑረዋል፡፡

እህት ኩባንያዎቹ በኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት መርሐ ግብራቸው በስፋት ከሚሳተፉባቸው ተግባራት አንዱ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን መደገፍ ሲሆን በተለይ ባለፉት 28 ዓመታት ውስጥ በሀገራችን የልማትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት ውስጥ አሻራቸውን ካስቀመጡት የግል የፋይናንስ ተቋማት መካከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡

# አዋሽ ባንክ እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራረሙ




የመግባቢያ ፊርማ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

አዋሽ ባንክ እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ሐምሌ 26/2014 ዓ.ም ተፈራርመዋል፡፡

ስምምነቱን የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው እና የኢመደአ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሹመቴ ግዛው ፈርመውታል፡፡

በስምምነቱ መሰረት ኢመደአ የአገሪቱን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ለሚያከናውናቸው ለሁለንተናዊ ሥራዎች የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ በአዋሽ ባንክ የሚደረግ ሲሆን፣ በሌላም በኩል የባንኩን የኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ድጋፍና እገዛ በኢመደአ በኩል እንደሚሰጥ ተጠቁሟል፡፡

የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በፊርማ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት ኢመደአ የፋይናንስ ሴክተሩን ጨምሮ ቁልፍ የሃገራችንን ተቋማት የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚሰራቸው ሥራዎች ከፍተኛ መሆናቸውን ጠቅሰው ይህንን ይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችል የፋይናንስ ድጋፍ ለኢመደአ መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡ በቀጣይም የሁለቱ ተቋማት የትብብርና የቅንጅት ሥራ ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

የኢመደአ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሹመቴ ግዛው በበኩላቸው ጠንካራ ሃገር መገንባት የሚቻለው ጠንካራ ተቋማትን መገንባት ሲቻል ነው ብለዋል፡፡ ስለሆነም ኢመደአ የአገራችንን የሳይበር ደህንነት የማስጠበቅ ዋና ተልዕኮውን ለማሳካት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች በጋራ ይሰራል ያሉት ዶ/ር ሹመቴ፣ ከአዋሽ ባንክ ጋር የተደረገው የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ፊርማም የአስተዳደሩ የትብብርና የቅንጅት ሥራ አንዱ አካል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

# አዋሽ ባንክ የታታሪዎቹ የስራ ፈጠራ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና አካሄደ

አዋሽ ባንክ ለሶስት ተከታታይ ቀናት አዲስ አበባ ድሬዳዋን ጨምሮ እና በተለያዩ ክልሎች ሲሰጥ የቆየውን የታታሪዎቹ የመጀመሪያ ዙር የስራ ፈጠራ ውድድር ስልጠና የምስክር ወረቀት በመስጠት አጠናቋል፡፡

የባንኩ ቺፍ ሪቴል ኤንድ ኤስኤምኢ ባንኪንግ ኦፊሰር አቶ ሄኖክ ተሰማ በስልጠናው የመዝጊያ ስነ-ስርአቱ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ አዋሽ ባንክ ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን ለማገዝ የተለያዩ አማራጮችን ነድፎ እየሰራ መሆኑንና ይህንንም ይበልጥ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል።










ለታታሪዎቹ የተሰጠው የመጀመሪያ ዙር ስልጠና በከፊል

# አዋሽ ባንክ በከባድ ዝናብ ቤታቸው ለወደመባቸው አርሶ አደሮች ድጋፍ አደረገ።




ለአርሶ አደሮች የተደረገው የድጋፍ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

ለማህበረሰብ መቆርቆርን አንኳር እሴቱ ያደረገው አዋሽ ባንክ በምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን ሜጫ ወረዳ በከባድ ዝናብ ቤታቸው ለወደመባቸው አርሶ አደሮች የቆርቆሮ ድጋፍ አድርጓል።

በሰሜን ሜጫ ወረዳ ሰኔ 4 እና ሰኔ 9/2014 ዓ.ም በጣለው በረዶ የቀላቀለ ዝናብ በ9 ቀበሌ 2ሺህ 631 አርሶ አደሮች የመኖሪያ ቤት፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በሌሎች ሰብሎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን የተናገሩት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አቶ አንተነህ ወንዱ፣ አዋሽ ባንክ 1ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር በሚሆን ወጪ ለተጎጂ አርሶ አደሮች ድጋፍ በማድረጉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

አዋሽ ባንክ ከምስረታው ጀምሮ የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረጉም ባሻገር በማንኛውም ወቅት ድንገተኛ አደጋዎች በሚያጋጥሙ ጊዜም ከማህበረሰቡ ጎን መቆሙን አጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዋሽ ባንክ ሰሜን ምዕራብ ሪጅን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሠረት አምበሉ በድጋፍ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ገልፀዋል፡፡

# አዋሽ ባንክ ከዘጠኝ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ጋር የብድር አቅርቦት ስምምነት አደረገ









የፊርማ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

አዋሽ ባንክ መካከለኛ፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኙ ከዘጠኝ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ጋር የብድር አቅርቦት ስምምነት አድርጓል፡፡ ባንኩ ይህን ስምምነት ያደረገው ዘጠኙ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትም፡- ቪዥን ፈንድ፣ ንስር፣ ቀንዲል፣ መተማመን፣ መክሊት፣ ዳይናሚክ፣ ዋሳሳ፣ ሃርቡ እና ፒስ ማይክሮፋይንስ አ.ማ ይገኙበታል።

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ሙፈርሃት ካሚል እንደተናገሩት የመካከለኛ፣ አነስተኛና ጥቃቅን የሥራ ዘርፎች ለሥራ ዕድል ፈጠራ ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት እና ለማህበራዊ ችግሮች ማቃለያ ከፍተኛ ሚና ቢኖራቸውም ያላቸውን እምቅ አቅም ተጠቅመው ወደ ሥራ ለመግባት የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት እንዳለባቸው በመግለፅ ባንኩ ላደረገው የብድር ድጋፍ ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትም ለዘርፉ እድገት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

# አዋሽ ባንክ የዲጂታል ትምህርት አስተዳደር መተግበሪያ ቴክኖሎጂን ይፋ አደረገ




የኢ-ስኩል የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

አዋሽ ባንክ በትምህርት ዘርፍ የዲጂታል ትምህርት አስተዳደር ስርዓት መተግበር የሚያስችለውን የኢ-ስኩል ማኔጅመንት ሲስተም ቴክኖሎጂን (E-School Management System Technology) የትምህርት ምኒስቴር ምንስትር ዲኤታ ክቡር ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ በተገኙበት ይፋ አድርጓል፡፡ ባንኩ ይህንን ዲጂታል ትምህርት አስተዳደር ስርዓት ሲተገብር ዋና አላማው የሀገራችን የትምህርት ጥራትን ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ በማድረግ በጎ ተፅዕኖ ለመፍጠር በማሰብ ነው፡፡

# አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመተባበር አዋሽ ሼባማይልስ ካርድን በስራ ላይ አዋለ




አቶ ክፍያለው ሽፈራው ዲፒዩቲ ቺፍ ዲጂታል ባንኪንግ ኦፕሬሽን ኢፊሰር ስምምነቱን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት

አዋሽ ባንክ እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባደረጉት የስራ ስምምነት አዋሽ ሼባማይልስ ካርድ በሚል በጥመረት ያሰሩትን ዴቢት ካርድ በስራ ላይ አዉለዋል።

በሁለቱ ተቋማት ጥምረት በስራ ላይ የዋለዉን የአዋሽ ሼባማይልስ ካርድን በአዋሽ ባንክ ፖስ ተርሚናሎች እንዲሁም በሁሉም የሌሎች ባንኮች ፖስ በመጠቀም የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችን መክፈል የሚቻል ሲሆን በካርዱ በአዋሽ ባንክ ፖስ ተርሚናሎች ለሚፈፀም ክፍያ ግን ደንበኞች ተጨማሪ ማይል የማግኘት ልዩ ዕድል ተጠቃሚ ይሆናሉ።

የአዋሽ ሼባማይልስ ካርድን በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች ማግኘት የሚቻል ሲሆን ካርዱን ለመውሰድና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሼባማይልስ ስጦታ ለማግኘት የሼባማይልስ አባልና የአዋሽ ባንክ ደንበኛ መሆን ያስፈልጋል።

በአዋሽ ሼባማይልስ ካርድ ለሚፈፅሙት ግብይትና ክፍያ በእያንዳንዱ መቶ ብር ስድስት ተጨማሪ ማይሎችን የሚያገኙ ሲሆን በስጦታ የሚያገኙት ተጨማሪ ማይልስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የስታር አሊያንስ አባል አየር መንገዶች ተቀባይነት አለዉ።

በአዋሽ ሼባማይልስ ካርድ ለሚፈፅሙት ግብይትና ክፍያ
አዋሽ ባንክ ቀደም ሲል ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የልማት ተቋማት ጋር ለመስራት የሚያስችሉትን የመግባቢያ ስምምነቶችን በመፈራረም ተቋማቱ የሚፈልጉትን የባንክ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

# Get Prepaid Card from Awash Bank




አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980
www.awashbank.com

# ዘመናዊ ስልክ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር የጥቃት አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

በዘመናዊ ስልኮች ላይ አብዛኛዎቹ የጥቃት መንሴዎች ከተጠቃሚዎች አመለካከት እና እውቀት ክፍተት፣ በመተግበሪያዎች ውስጥ ባለ ክፍተት እና የዘመናዊ ስልኮችንና መተግበሪያዎችን ኢላማ ያደረጉ ተንኮል አዘል መተግበሪያዎች ምክንያት የሚከሰቱ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከታች የተዘረዘሩ የአጠቃቀም ክፍተቶች ስማርት ስልኮቻችን ለጥቃት እንዲጋለጡ ያደርጋሉ።

- የማረጋገጫ መዋቅሮች ስህተት: ከአካውንት ጋር በተያያዘ ጠንካራ ያልሆነ የይለፍ-ቃል መጠቀም አንዱ የጥቃት መንስኤ ሲሆን፤ሌላው ደግሞ ጠንካራ ያልሆነ ወይም የጊዜ ገደብ የሌለው የአንድ ጊዜ የማረጋገጫ ኮድ በተለይም እንደ የSMS OTP ወይም የጥሪ OTP በመተግበሪያዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ አጥቂዎች የተጠቃሚዎችን አካውንት በመገመት ሊጠልፉ ይችላሉ።
- የዳታ ተጋላጭነት (leakage)፡ ይህ የጥቃት አይነት በዋናነት ተጠቃሚዎች ለመተግበሪያዎች በሚሰጧቸው ያለገደብ ፈቃድ ምክንያት የሚከሰት ሲሆን ተንኮል አዘል መተግበሪያዎቹ ተጠቃሚዎችን በመሰለል የስልክ የጥሪ፣ የመልዕክት፣ የምስል፣ የዶክመንት ወዘተ መረጃዎችን ወይም የመተግበሪያዎች (የአካውንት መለያዎችን፣ ቶከኖችን፣ የስልክ መለያ ኮዶችን፣ የማረጋገጫ ኮዶችን ወዘተ) አፈትልኮ በማስወጣትና በመስረቅ፣ በመላክ የሚደርስ የጥቃት አይነት ነው።
- የመረጃ አቀማመጥ ስህተት፣ ይህ በዋናነት በመተግበሪያዎች ሚስጢራዊ የሆኑ ዳታን (እንደ ይለፍ ቃል፣ ቶከን) ሳይመሰጥሩ ከስልኩ በዳታ ቤዝ፣ በውስጣዊ ዲስክ ወይም በሚሰኩ የውጫዊ ዳታ ማስቀመጫ ቁሶች (external data storage device) ማስቀመጥ በተንኮል አዘል መተግበሪያዎች ሊነበቡ፣ ሊቀየሩ፣ ሊሰረቁ ይችላሉ።
- የስልኮችን ኦፐሬቲንግ ሲስተም ከገደብ ነጻ ማድረግ፣ ይህ ለምሳሌ በአንድሮይድ ሩቲንግ (Rooting) የሚባል ሲሆን ይህም ለመተግበሪያዎች ወይም ለተጠቃሚው የሩት ተጠቃሚነት ሙሉ ነጻ ፈቃድ መስጠት ማለት ነው። ሩት ፈቃድን መስጠት የኦፐሬትንግ ሲስተሙ የደህንነት ማስጠበቂያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ የሚያደርግ ሲሆን ተንኮል አዘል መተግበሪያዎች ይህን በመጠቀም የሌሎችን መተግበሪያዎች ዳታ መስረቅ፣ አሰራሮችን ማወክ እንዲሁም ስልኩን ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል።
- ደህንነቱ ያልተጠበቀ ዋይ ፋይ መጠቀም፤ አጥቂዎች ነጻ የሆነ ዋይፋይ ወይም ፌክ አክሰስ ፖይንት እና የኔትዎርክ መተንተኛ መተግበሪያዎችን በመጠቀም የተጠቃሚዎችን የሶሻል ሚዲያ፣ የባንክና ፋይናንስ እንዲሁም የሌሎች መተግበሪያዎችን መለያዎች፣ ቶከኖች ለመስረቅ የሚጠቀሙበት የጥቃት አይነት ነው።
- ፊሺንግ (ወይም ማህበራዊ ምህንድስና) ፣ ተጠቃሚዎች የሲስተሞቻቸውን አካውንቶች እንደ ኢ-ሜይል የሶሻል ሚዲያንም ጨምሮ የሚቆጣጠሩበት ወይም የሚቀመጡት ስልኮቻቸው ላይ እንደመሆኑ መጠን ለብዙ አይነት የማህበራዊ ምህንድስና የጥቃት ዘዴዎች ሰለባ ይሆናሉ።
- ጠንካራ ያልሆነ የምስጠራ ዘዴ፡ ይህ በመተግበሪያዎች ባለ ወይም በክሊየንት ሰርቨር መዋቅር ውስጥ ባለ የምስጠራ ድክመት ወይም ክፍተት ያለበት የምስጠራ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ በማድረግ የሚመጣ ሲሆን በተገማች ወይም ጠንካራ ባልሆነ ዘዴ የተመሳጠሩ መረጃዎችን በመስበር ሊያነቡ፣ ሊሰርቁ ወይም ሊቀይሩ ይችላሉ።
- የመተግበሪያዎች (የኦፐሬቲንግ ሲስተምን ጨምሮ) አለመዘመን፣
- ደህንነቱ ያልተጠበቀ መተግበሪያን በመጠቀም፣ የመረጃ መንታፊዎች ጌሞችን፣ ወይም ትክክለኛ መተግበሪያን በመገልበጥ ተንኮል አዘል ጽሁፎችን በማስረጽ ወይም በማስገባት እና በማህበራዊ የትስስር ገጾች ወይም ሌሎች ድሮች ላይ በማስቀመጥ ተጠቃሚዎችን በማታለል እንዲጭኑ በማስደረግ ቋሚ የሆነ የሩቅ መር የቁጥጥር ስርዓትን (remotely controlled system) በመተግበር እና ሌሎችን አይነት መጠነ ሰፊ ጥቃቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ።

# በዘመናዊ ስልኮች ላይ ያሉ ክፍተቶች እና የሚያመጡት አሉታዊ ተፅዕኖዎች

በዘመናዊ ስልኮች ላይ አብዛኛዎቹ የጥቃት መንሴዎች ከተጠቃሚዎች አመለካከት እና እውቀት ክፍተት፣ በመተግበሪያዎች ውስጥ ባለ ክፍተት እና የዘመናዊ ስልኮችንና መተግበሪያዎችን ኢላማ ያደረጉ ተንኮል አዘል መተግበሪያዎች ምክንያት የሚከሰቱ ናቸው። በዘመናዊ ስልኮች ያሉ ክፍተቶች የሚያሚጡት አሉታዊ ተፅዕኖዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከመተግበሪያዎች (የድር መተግበሪያዎችን ጨምሮ) በተለይም በሶሻል ሚዲያ ባሉ ሲስተሞች የመለያ ጥቃቶችን ተከትሎ ተጠቃሚዎች የግል መረጃዎቻቸው ለስርቆት እና ለምዝበራ የሚያጋልጥ ሲሆን፤ ይህም በማህበረሰብ፣ በቅርብ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ ብሎም በስራ ሁኔታ ላይ ከባድ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል።
- ከዘመናዊ ስልኮችና የኦንላይን ክፍያ ስርዓት መስፋፋት አንጻር የባንክና የፋይናንስ ተቋማት መተግበሪያዎች ብዙውን ጊዜ በአጥቂዎች ኢላማ ውስጥ ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለጥቃት ሰለባ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህም ተጠቃሚዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚጎዳ ይሆናል።
- ከስልኮቹ መዘመንና መራቀቅ ጋር ተያይዞ ተጠቃሚዎች የሚኖራቸውን የኮምፒውተርም ሆነ የሌሎች መሳሪያዎችን መረጃ (የአካውንት መለያዎችን ጨምሮ) ለማስቀመጥ ምቹ እና ተመራጭ ናቸው፡፡ በመሆኑም በስልኮች ላይ በሚከሰቱት ጥቃቶች ምክንያት ሙሉ የአካውንቶቻቸው መለያዎች ሊመዘበሩ ስለሚችሉ ተጠቃሚዎችን ችግር ውስጥ የሚጥሉ ይሆናል።
- ተጠቃሚዎች ከሌሎች መሳሪያዎች (በተለይ የበይነመረብ ቴክኖሎጂዎች) ጋር መስተጋብራዊ ግንኙነት መፍጠር እንዲችሉ ስለሚያደርጉ የስልኮቹ በጥቃት ኢላማ ውስጥ መውደቅ እንዲሁ ተፈጥሮ የነበረውን ግንኙነት ስለሚያውክ በንብረት ላይም ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ።
- ተጠቃሚዎች ስራቸውን ለማከናወን እንደሚጠቀሙት ሲስተም ወይም መተግበሪያ አይነት የሚከሰቱ ጥቃቶች ስራቸውን ሊያስተጓጉል፣ ሊያውክ ብሎም ሊያበላሽና ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።
- ተጠቃሚዎች በሚደርስባቸው ጥቃቶች ምክንያትም የስልኮቹን ስርዓትና የአሰራር ሂደት ወደ መጥላት እና ወደ መፍራት ሊወስዳቸው ስለሚችል አሁን ላይ ላሉ የቴክኖሎጂ የአሰራር ሂደቶች አብረው ለመሄድ ይቸገራሉ።

በአጠቃላይ በዘመናዊ ስልኮች (smart phone) ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶች ተጠቃሚዎች ላይ የሞራል፣ማህበረሰባዊ፣ የፋይናንስ፣ የስራ እና የመሳሰሉ ከባድ ቀውሶችን ሊያስከትሉባቸው ይችላሉ፡፡

https://www.insa.gov.et/web/en/cyber-security1
source: INSA (Information Network Security Agency) Website.

# PROVERBS & QUOTES

**“The most difficult thing is the decision to act, the rest is merely tenacity.”**

Amelia Earhart

**“Permit yourself to change your mind when something is no longer working for you.”**

Nedra Glover Tawwab

**“Though no one can go back and make a brand new start, anyone can start from now and make a brand new ending.”**

Carl Bard

**“'First things first' might be a cliche, but it's a useful one that means prioritizing what matters most to you and believing there is no wrong answer.”**

Stacey Abrams

# PHOTO REEL


ANNUAL
MANAGEMENT
MEETING








ANNUAL
MANAGEMENT






ANNUAL
MANAGEMENT












ለታታሪዎቹ የተሰጠው የመጀመሪያ ዙር ስልጠና የመዝጊያ ፕሮግራም በከፊል















የመጀመሪያ ዙር የታታሪዎች ስልጠና ተሳታፊዎች ፎቶ በከፊል

# መደበኛ እና ሌሎችም

## የቁጠባ አማራጮች
## ከአዋሽ ባንክ




አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980
www.awashbank.com

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River




# ሙዳይ

## የቁጠባ ሳጥን አገልግሎት